ጽርሐ አርያም ቅድስት ሥላሴ
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
ሚኒያፖሊስ ሚኒሶታ

Tserha Aryam Kidist Selassie
Ethiopian Orthodox Tewahedo Church
Minneapolis, Minnesota

ቀን: ኅዳር ፫/፳፻፲፭ ዓ.ም.
ቁጥር: 012/11/2015

**በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!**
**ንቁ፤ በሃይማኖት ቁሙ፤ ጎልምሱ ጠንከሩ። በእናንተ ዘንድ ሁሉ በፍቅር ይሁን። ፩ ቆሮ. ፲፮፥፲፫**

የጽርሐ አርያም ቅድስት ሥላሴ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ ይኽንን መግለጫ ለመስጠት የፈለገበት ምክንያት ሰሞኑን በአካባቢያችን የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት የሆኑ ጳጳሳት በሲኖዶስ ሥር ከሌሉ ጋር በማበር ከቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ በተቃራኒ በመሆን ያስተላለፉትን ትምህርት መሰል መግለጫ ከሃይማኖታዊ አስተምህሮ ውጪ ከእውነታው የራቀ መሆኑን ለምእመናኑ ለማሳወቅና ምእመናን እንዲህ ያለውን የሐሰት ምስክርነት ተቀብለው ካሉበት የሃይማኖት ጽናት እንዳይናወጡ ለማድረግ ነው።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በአምስቱ አዕማደ ምሥጢራትና በሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ላይ ከፍተኛ ጥንቃቄ የምታደርገው አስቀድሞ እነዚህን ምሥጢራት ሊፈጽሙ የሚችሉት ሥልጣነ ክህነት ያላቸው ካህናት ብቻ መሆናቸውን አጥብቃ በማስተማር ነው። ሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ተብለው የተጠሩት ምሥጢራት በካህናት ብቻ የሚፈጸሙ እንጂ በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ጥሰትና በሐይማኖት ግድየለሽነት በተነካ ሥልጣነ ክህነታቸው በተያዘ የሚፈጸሙ ምሥጢራት አይደሉም። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የዲያብሎስን አሠራር እየተዋጋች በድል ላይ ድል እያገኘች ዛሬ ለደረሰችበት ደረጃ የደረሰችው ሥርዓተ ሃይማኖቷን አንኮታኩቶ ለመጣል በየዘመናቱ የተነሡትን መናፍቃን በአግባቡ ተሟግታ፣ ታግላና አሸንፋ ምሥጢረ ክህነትን በመጠበቅዋ ነው። አንዲት እምነት፣ አንዲት ሃይማኖት፣ አንዲት ጥምቀት በማለት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የጻፈውን ቃል በማመን ፕሮቴስታንቱም፣ ካቶሊኩም፣ ጆሆቫውም፣ ሚሲዮናውያኑም እንደ እምነታቸው ያጠምቃሉ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ልጆቿን በአርባና በሰማንያ ቀናት በማጥመቅ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ የምታደርጋቸው በቀደመችውና በትክክለኛው እምነት ውስጥ ሆነው አምላካችን ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያት ያስተማራቸውን ሐዋርያትም ሥልጣነ ክህነት በመስጠት በየዘመኑ ለተተኪዎቻቸው ያስተማሩትን እርከኑ የተጠበቀለትንና ያልተቋረጠ ቅብብሎሽን መሠረቷ በማድረግ ነው።

ሥልጣነ ክህነታቸው ከተያዘባቸው ጋር በማገልገል ላይ ካሉት ከሊቃነ ጳጳሳቱ እንደተገለጸው የተደገመ ጥምቀት እንደ ሻወር የሚቆጠረው ሥልጣነ ክህነት ያላቸው አባ እገሌ ያጠመቁትን ሌላ ሥልጣነ ክህነት ያላቸው አባ እገሌ ሲደግሙት ነው። ሥልጣነ ክህነት የሌለው ደፋር አጠመቅሁኝ ያለውን እንደ ሻወር ቆጥሮ ሥልጣነ ክህነት ባለው ካህን ማስጠመቅ ግን ሃይማኖት ማጽናትና አንዲት ጥምቀት የተባለችውን ትዕዛዝ መፈጸም ነው። አሁንም እንደግመዋለን ሥልጣነ ክህነት የሌለውና ፈቃዱን የተቀማ እንደ ቤተ ክርስቲያኗም ቀኖና መስቀል ከማሳለም፣ ቅዱስ ቁርባን ከማቀበል፣ ታቦት ከመዳሰስ፣ ሥርዓተ ጥምቀት ከመፈጸምና ሌሎችም በካህናት ብቻ ሊፈጸሙ የሚገባቸውን እንዳያደርግ እግድ የተጣለበት ሰው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብቻ ስለተገኘ አጥምቄያለሁ ብሎ ቢናገር መንፈስ ቅዱስ የተለየው ምሥጢራትን ለመፈጸም እያሰበ ነውና ጥምቀቱ እንደማይሠራለት በገሐድ የታወቀ ነው።

2601 Minnehaha Ave. S. Minneapolis, MN 55406 taksmnoffice@gmail.com

ክህነት ሳይኖራቸው የክህነት አገልግሎትን እንፈጽማለን ባሉ የጥፋት ሰዎች ላይ የደረሰውን ቅጣት አሪት ዘኍልቁ ምዕራፍ አሥራ ስድስትን ማንበቡ ብቻ በቂ ይሆናል። እንደዚያማ ባይሆን ቤተ ክርስቲያናችን ከሌላ እምነት የሚመጡትን ተቀብላና አስተምራ ባላጠመቀቻቸው ነበር። በመሆኑም ይኸን ሕግ ያጸኑልን አባቶቻችን **"የመናፍቃንን ጥምቀት የተቀበለ ወይም ቁርባናቸውን የተቀበለ ወይም ከእነርሱ ጋር አብሮ የሚጸልይ ቄስ ይሻር።"** በማለት ጽፈዋል። በመቀጠልም **"በታወቀች ኃጢአቱ በእርግጥ የተሻረ ቄስ ወይም ዲያቆን ቢኖር ከዚህም በኋላ ቀድሞ ሳይሻር በሰሞኑ ወራት ይሠራው የነበረውን የአገልግሎት ሥራ ተደፋፍሮ ቢሠራ ከቤተ ክርስቲያን ፈጽሞ ይለይ፤ ሥራውንም እያወቀ ከርሱ ጋር አንድ የሆነ ሁሉ ይሻር።"** ይላል። ፍትሐ ነገሥት ፪፻፳፬ እና ፪፻፳፫።

ታዲያ መልእክቱ ሥልጣነ ክህነትህን ሥልጣነ ክህነት ሊይዝ የሚገባው የከፍሉ ሊቀ ጳጳስ ስለያዘው የቀደመውን የአገልግሎት ሥራ ተው፤ መደፋፈር የለብህም፤ ምእመናኑንም አታሳዝን መሆን ሲገባው በሕዝብ መካከል ቆሞ ኃጢአትን ማደፋፈርና በርታ ቀጥልበት ማለት የተወሰነች ደቂቃ የዐውደ ምሕረት ላይ ደስታ ታመጣለች እንጂ ዘለቄታዊ እንደማትሆን አይዞህ ባዩም አይዞህ ተባዩም ያውቁታል። ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ **ወንድም ወይም እኅት ራቁታቸውን ቢሆኑ የዕለት ምግብንም ቢያጡ፥ ከእናንተ አንዱም "በደኅና ሂዱ፥ እሳት ሙቁ፥ ጥገቡም" ቢላቸው ለሰውነት ግን የሚያስፈልጉትን ባትሰጡአቸው ምን ይጠቅማቸዋል?** ይለናል። ሥልጣነ ክህነቱ ተገፎ ራቁቱን የሆነውን ሰው በንስሐ አሳጥቦ የተገፈፈች የክህነትን ክብር አልብሶ እርቃኑን መሸፈን ሲገባ ራቁቱን የቆመውን ሰው ራቁትህን አይደለህም ማለቱ ጥቅሙ ምንድን ነው?

"ዋናውን መልእክት አስተላልፈናል፤ ደስ ብሎኻል ወይ?" ብሎ ከመጠየቅ ቤተ ክርስቲያንም፣ ሕዝቡም፣ ተማሪውም አስተማሪውም እንዲረጋ ሥልጣነ ክህነቱን በተገቢው መልክ ማስመለስና ዘላለማዊ ሰላም መፍጠር እንጂ መምጣታችን ካልቀረ በዐውደ ምሕረቱ ላይ ይኼን ያህል ብለናል ብንል አይጠቅምም። ዛሬ ያላሉትን ልጓም ነገ ማጥበቅ ይከብዳል። በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ አሥር ላይ ያለው ዋናው ኃይለ ቃል ሁለት ሁለት ሆነው እንደ በጎች በተኩላዎች መካከል መላካቸው ብቻ ሳይሆን በቁጥር አሥራ-ስድስት ላይ **የሚሰማችሁ እኔን ይሰማል፥ እናንተንም የጣለ እኔን ይጥላል፤ እኔንም የጣለ የላከኝን ይጥላል።** የሚለው ነው። ታዲያ እነርሱን የወደደ የእነርሱን መንገድ ይከተላል እንጂ እንዴት እረኞቹ የበጎቹን መንገድ ይከተላሉ? በመልካም ስፍራ ማሰማራት የሚገባው እረኛው እንጂ ቦታ መርጠው ወዳሰኛቸው መንገድ የሚሄዱት በጎች ሊሆኑ አይገባቸውም። በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ፤ ይከተሉኛማል ማለት ሊቀ ጳጳሳቱንም ልጆቻቸው ድምፃቸውን ይሰማሉ፤ ይከተሉማቸዋል ማለት ነው። መመሪያና ሕግ አውጥተው እራሳቸው ካፀደቁት ውሳኔ ላይ ስለምን ይጣላሉ? ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ **ከአንድ አፍ በረከትና መርገም ይወጣሉ። ወንድሞቼ ሆይ፥ ይህ እንዲህ ሊሆን አይገባም። ምንጭስ ከአንድ አፍ የሚጣፍጥንና የሚመርን ውኃ ያመነጫልን? ያዕቆብ** ፫፡፲፩ እንዳለ እንዴት ሕዝብን ከሚመሩ አባቶቻችን ሁለት ቃል እንሰማለን? መንገዳቸውን ሳንከተል ስንቀር የአባትነት አደራ በመስጠት የቤተ ክርስቲያን መንገድ ሊሆን የሚገባው እንዲህ ነው በማለት ምክር ይሰጡናል። ቃላቸውን ተግብረን ስንገኝ ከቤት እንደወጣን አድርገው በማየት ያለ ሥርዓት የሚሄዱትን ከመገሰጽ መንገዳቸውን የቀና በማስመሰል አይዟችሁ ሲሉ ይደመጣሉ። ይህ እንዲህ ከሆነ ጣፋጭም

መራራም ከአንድ አፍ መውጣቱ ትክክል ነው ማለት ግን ይከብደናል። አቡነ ዳንኤል በመልእክታቸው "**ከዚህ የትም እንዳትሄዱ እዚህ ባላችሁበት ሆናችሁ ቤተ ክርስቲያን ታውቃችኋለች፣ ቅዱስ ሲኖዶስም ያውቃችኋል**" ሲሉ ተደምጠዋል። የሚገርመው ግን እርሳቸው በተሳተፉበትና አብረው ባጸደቁት የጥቅምት ወር ፳፻፲ ዓ.ም. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የ፴፮ኛው አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ካወጣው ሃያ ሦስት የአቋም መግለጫ ውሳኔ ላይ በቁጥር ሦስት እና አሥራ-ዘጠኝ ላይ የወጣውን የአቋም መግለጫ እንደተቃወሙ ባለማወቃቸው ነው። የመግለጫውም ሙሉ ቃል እንዲህ ይላል፡-

፫) የቅዱስ ሲኖዶስን ሉዓላዊነት የሚጋፉ፣ ለቤተ ክርስቲያን ማእከላዊ አመራር አንታዘዝም የሚሉ፣ ቤተ ክህነት ምን አገባው፣ ሀገረ ስብከት ምን አገባው፣ ቅዱስ ሲኖዶስ ምን አገባው፣ የጠቅላይ ቤተ ክህነት አስተዳደራዊ መዋቅር ምን አድርጎልናል በሚል የማደናገሪያ ስልት መዋቅርን የሚንዱ ችግሮች በከፍተኛ ፍጥነትና ብዛት በተደራጀና በተጠና ስልት በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር በከፍተኛ ፍጥነት እያደጉ ስለሆነ ቅዱስ ሲኖዶስ ለጉዳዩ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት እንዲወያበትና መፍትሔ እንዲሰጠው ለዘመናት ጸንቶ የቆየውን የቤተ ክርስቲያንን መዋቅር እንዲያስጠብቅ በከፍተኛ ስሜት እንጠይቃለን።

፲፱) የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ሲኖዶሳዊ መሆኑ ይታወቃል። ይሁን እንጂ በአንዳንድ አካባቢዎች እንደ ፕሮቴስታንታዊ ተሐድሶ አብያተ ክርስቲያናት ከሲኖዶሳዊ መዋቅር የወጣ ቀኖናዊ ትውፊትን ያልጠበቀና ኢክርስቲያናዊ ኢኦርቶዶክሳዊ የሆነ ገለልተኛ ቅንጅት በመፍጠር ምእመናንን በሚያደናግሩ አካላት ዙሪያ ቅዱስ ሲኖዶስ አስቸኳይ መፍትሔ እንዲያስቀምጥለት ለተግባራዊነቱም የበኩላችንን ለማድረግ ቃል እንገባለን።

ታዲያ ይኽ እንዲህ ሆኖ ሳለ ቀኖና ቤተ ክርስቲያንንና ሥርዓትን ጥሰው በገዛ ፈቃዳቸው ከቤተ ክርስቲያኒቱ ሃይማኖታዊ አመራር ከወጡት ጋር ወግነው እንዲህ ያለ ቃል ማውጣት ስለምን አስፈለጋቸው? መልሱን ለእርሳቸውና ጉዳዩ ለሚመለከተው ለቅዱስ ሲኖዶስ ትተነዋል። አሁንም በተደጋጋሚ የሚያነሡት የዕርቅ ጉዳይ ባለፈው መግለጫችን ላይ እንደገለጽነው ጥሉ ከጽርሐ አርያም ቅድስት ሥላሴ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ካህናትና ምእመናን ጋር ሳይሆን የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ጉዳይ በመሆኑ ይኽንን ማየት የሚገባቸው ክፍሎች እያዩት መሆናቸውን በድጋሚ እንገልጻለን።

በመጨረሻም ምእመናን እንድትረዱ የምንፈልገው እንዲህ ዓይነት ፈተናዎች በተደጋጋሚ እንደሚከሰቱ አውቃችሁ በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ጸንታችሁ እንድትቆሙ እያሳሰብን በዚህም ዙሪያ በዐውደ ምሕረት ተከታታይ ትምህርት በቤተ ክርስቲያን መምህራን የሚሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን።

የጽርሐ አርያም ቅድስት ሥላሴ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ